25ኛ ዓመት ቁጥር 157
አሶሳ

ሐምሌ 27/ 2010 ዓ.ም

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**

**ልሣነ ህግ ጋዜጣ፣**

***በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት***

***ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ አዋጅ፣***

ፖ.ሳ.ቁ. 293

ያንዱ ዋጋ------------

# አዋጅ ቁጥር 157/2010 ዓ.ም

## በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት መካከል የተደረገ የሁለትዮሽ የሠላምና የጋራ ልማት ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ.

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት መካከል የሁለትዮሽ የሠላምና የጋራ ልማት ትብብር ስምምነት ህዳር 26 ቀን 2010 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ የተፈረመ ስለሆነ፣

የተፈረመው የሁለትዮሽ የሠላምና የጋራ ልማት ትብብር ስምምነት ለክልል መንግሥታት ህግ አውጪ ም/ቤት ቀርቦ መጽድቅ እንዳለበት በተሻሻለው የክልሉ ህገ- መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3.3 የሚደነግግ በመሆኑ፣

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

## አንቀጽ 1፣

## አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሁለትዮሽ የሠላምና የጋራ የልማት ትብብር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር 157/2010 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 2፣

## ስምምነቱ ስለመጽደቁ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መካከል ህዳር 26 /2010 ዓ.ም በቢሾፍቱ ከተማ የተፈረመው ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## አንቀጽ 3፣

## ስምምነቱን ሥራ ላይ ስለማዋል

የሚመለከታቸው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት አካላት ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲያውሉ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቷቸዋል፡፡

## አንቀጽ 4፣

## አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ስምምነቱ ከተፈረመበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ

ሐምሌ 27/2010 ዓ.ም

አሻድሊ ሀሰን አልአጅብ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት